የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራአንደኛ ዓመት ቁጥር ፶ አዲስ አበባ ሰኔ ፳፫ ቀን ፲፱፻፺፯

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

11th Year No. 50
ADDIS ABABA- 30th June, 2005


ማውጫ


አዋጅ ቁጥር ፬፻፷/፲፱፻፺፯ ዓ.ም

ከኦስትሪያ ሪፐብሊክ መንግሥት ጋር ኢንቨስትመንትን ለማበረታታትና ጥበቃ ለመስጠት የተደረገውን ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ... ገጽ ፫ሺ፩፻፷፫


**CONTENTS**


**Proclamation No. 460/2005**

Investment Promotion and Protection Agreement with the Republic of Austria Ratification Proclamation.......... Page 3163


## አዋጅ ቁጥር ፬፻፷/፲፱፻፺፯

## በኦስትሪያ ሪፐብሊክ መንግሥት ጋር ኢንቨስትመንትን ለማበረታታትና ጥበቃ ለመስጠት የተፈረመውን ስምምነት ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥትና በኦስትሪያ ሪፐብሊክ መንግሥት መካከል ኢንቨስትመንትን ለማበረታታትና ጥበቃ ለመስጠት የሚያስችል ስምምነት ኅዳር ፫ ቀን ፲፱፻፺፯ ዓ.ም በቬይና ከተማ የተፈረመ በመሆኑ፣

ስምምነቱ ሥራ ላይ የሚውለው በተዋዋይ ሀገሮች ሕጎች መሠረት ስምምነቱ መጽደቁን የሚያረጋግጡ ሰነዶች በዲፕሎማቲክ አካላት አማካኝነት ልውውጥ ከተደረገ በኋላ እንደሆነ በስምምነቱ በመገለፁ፣

ይህንኑ ስምምነት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሰኔ ፳፫ ቀን ፲፱፻፺፯ ዓ.ም ባደረገው ስብሰባ ያፀደቀው ስለሆነ፣

በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ ፶፭/፩/ እና /፲፪/ መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "ከኦስትሪያ ሪፐብሊክ መንግሥት ጋር ኢንቨስትመንትን ለማበረታታትና ጥበቃ ለመስጠት የተደረገውን ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ ቁጥር ፬፻፷/፲፱፻፺፯" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

## PROCLAMATION NO. 460/2005.

## A PROCLAMATION TO RATIFY THE AGREEMENT SIGNED ON THE PROMOTION AND PROTECTION OF INVESTMENTS WITH THE GOVERNMENT OF THE REPUBLIC OF AUSTRIA

**WHEREAS,** the Agreement on Promotion and Protection of Investments between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Republic of Austria is signed in Vienna on 12th November 2004;

**WHEREAS,** it is stipulated in the Agreement that it shall enter into force on the date of exchange of instruments of ratification through diplomatic channels;

**WHEREAS,** the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified said Agreement at its session held on the 30th day of June, 2005;

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Article 55 Sub Articles (1) and (12) of the Constitution, it is hereb, proclaimed as follows;

### 1. Short Title

This Proclamation may be cited as "Investment Promotion and Protection Agreement with the Republic of Austria Ratification Proclamation No.460/2005."


ያንዱ ዋጋ 2·30
Unit Price

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

**፪. ስምምነቱ ስለመፅደቅ**

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በኦስትሪያ ሪፐብሊክ መካከል ኢንቨስትመንትን ለማበረታታትና ጥበቃ ለመስጠት በቪየና ከተማ፣ ኅዳር ፫ ቀን ፲፱፻፺፯ ዓ.ም የተፈረመው ስምምነት ፀድቋል፡፡

**፫. የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን ኃላፊነት**

የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን ስምምነቱን በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ኃላፊነት ተሰጥቶታል፡፡

**፬. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ ከሰኔ ፳፫ ቀን ፲፱፻፺፯ ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ሰኔ ፳፫ ቀን ፲፱፻፺፯ ዓ.ም.

ግርማ ወልደጊዮርጊስ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት

**2. Ratification of the Agreement**

The Agreement on the Promotion and Protection of Investments signed in Vienna on 12th November 2004 between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Republic of Austria is ratified;

**3. Responsibility of the Ethiopian Investment Commission**

The Ethiopian Investment Commission is hereby empowered to implement this Agreement.

**4. Effective Date**

The Proclamation shall enter into force as of 30th day of June, 2005.

**Done at Addis Ababa, the 30th day of June, 2005**

**GIRMA WOLDEGIORGIS**
**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት